# መመሪያ ቁጥር 1093/2017

## የፀረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ

የፀረ ተባይ ምርት በሰው ጤና እና በአካባቢላይ የሚያደርስው አሉታዊ ተፅዕኖ ዝቅተኛ ኢንዲሆን እና ውጤታማነቱ የተሻለ እንዲሆን፣ ህጋዊ መሰረት ያለው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በማስፈለጉ፤

ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን እና አለመግባባቶችን ግልፅ እና ሕግን መሰረት ያደረገ ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ፤

የግብርና ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል ፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የፀረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ ቁጥር: 1093/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"የፀረ-ተባይ ምዝገባ"** ማለት የፀረ-ተባይ ጥራት፣ ውጤታማነትንና ደህንነትን በመስክና በቤተ ሙከራ የሚረጋገጥበት እና የቀረበው መረጃ የሚገመገምበትና እና የሚመዘገብበት ሂደት ነው፤
   2) **"የፀረ-ተባይ አስመዝጋቢ"** ማለት የፀረ-ተባይ አምራች ወይም አዘጋጅ ሆኖ የፀረ ተባይን ፍቱንነት ጥራትና ደህንነት መረጃዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያቀርብ ሰው ነው፤

3) **"የምዝገባ ሰርተፊኬት"** ማለት የምዝገባ መስፈርቶቹ መሟላታቸው ተረጋግጦ ለተመዘገበው ፀረ-ተባይ ለአምራቹ ወይም ለአዘጋጁ የሚሰጥ የአምስት ዓመት ቆይታ ጊዜ ያለው የምስክር ወረቀት ነው፤

4) **"የፀረ-ተባይ ዶሴ"** ማለት ለፀረተባይ ምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ በፀረ-ተባይ አስመዝጋቢው በኩል ምዝገባውን ለሚያከናውነው አካል የሚቀርብ የሰነዶች ስብስብ ነው፤

5) **"የአዲስ ግኝት ፀረ-ተባይ ዋነኛ ንጥረ ነገር"** ማለት በአከባቢና በጤና ላይ ስጋቱ አነስተኛ የሆነ ወይም ለተቀናጀ የተባይ መከላከያ ዘዴ አገልግሎት የሚውል ውጤታማነቱ እና ተፈላጊነቱ በሀገር ውስጥ የተረጋገጠ እና በሀገር ውስጥ እስከአሁን ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ነው፤

6) **"ቀዳሚ መረጃ ምንጭ"** ማለት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በራሱ ወይም ፈቃድ ከሰጠው የግብርና ምርምር ተቋም ወይም ግብርና ዩንቨርስቲ የተዘጋጀ ከፀረ ተባይ ፍቱንነት ጋር የተያያዙ ሪፖርትን የሚያካትት ነው፤

7) **"ተከታይ የመረጃ ምንጭ"** ማለት ባለስልጣን መስሪያቤቱ በራሱ ወይም ፈቃድ ከሰጠው የግብርና ምርምር ተቋም ወይም ግብርና ዩንቨርስቲዎች ውጪ በሆነ በሀገር ወስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የሚገኝ አግባብ ባለው አካል የተዘጋጀ ከፀረ ተባይ ፍቱንነት እና ውጤታማነት ጋር ተዛማጅነት ያለው ሙከራ ውጤት ሪፖርት፣ ጥናታዊ ፅሑፍ፣ ለህዝብ ተደራሽ የሆነ የህትመት ውጤትን የሚያካትት ነው፤

8) **"የታለመ ሰብል"** ማለት ፀረ ተባዩ ከተባይ እንዲከላከልለት የታቀደው እና የፍቱንነት ሙከራ የሚካሄድበት የሰብል ዓይነት ነው፤

9) **“አቅራቢያ ሰብል”** ማለት የታለመው ሰብል በሚበቅልበት በተመሳሳይ ጊዜ በአቅራቢያ በኩታ ገጠም ማሳ የተዘራ ወይም የበቀለ ሰብል ነው፤

10)**“ተከታይ ሰብል”** ማለት የታለመው ሰብል ምርት ወቅት አብቅቶ በተመሳሳይ መሬት ላይ ቀጥሎ የተዘራ ወይም የበቀለ ሰብል ነው፤

11)**“ቅድመ ማረጋገጫ ሙከራ ልኬት”** ማለት አንድ ፀረ-ተባይ ካለው ጠቀሜታና የጎንዮሽ ጉዳት አንፃር በዝቅተኛ መጠን የሚፈለገውን የውጤታማነት ግብ ማሳካትና ያለው ብቃት የሚገመገምበት የሙከራ ዓይነት ነው፤

12)**“የዋና ንጥረ ነገር የፊዚካል ባህሪያት”** ማለት እያንዳንዱ የዝግጅት ምርት እንደ ቅመራው ዓይነት የሚኖረው የተለየ ባህሪ እንደተጠበቀ ሆኖ አካላዊ ሁኔታ፣ ቀለም፣ ሽታ፣መጠነ-ቁስ፣ የትነት የመከለሻ ቁስ አካላት የሥሪት ይዘት መጠነ ገደብ በመቶኛ ፣ ግፊት፣በውኃ እና በካርቦናማ አሟሚዎች የሙሙት መጠን፣ የመለየያ እና የፍርሰት ሙቀት መጠን፣ የቅልጠት እና የፍሌት ልኬትን ይጨምራል፣

13)**“የዋና ንጥረ ነገር ኬሚካላዊ ባህሪያት”** ማለት ቁስ አካሉ የያዘው የዋና ንጥረ ነገር፤ የምስሎታ እና የአብራዥ ይዘትና መጠነ ገደብ በመቶኛ መግለጽን ያጠቃልላል፤

14) **“ማረጋገጫ ሙከራ”** ማለት የቅደመ ማረጋገጫ ሂደቱን ካለፈ በኂላ ከሌላ ለተመሳሳይ አገልግሎት ከሚውል ፀረ-ተባይ ጋር የሚነጻጸር ሙከራ ነው፤

15)**“የመቆጣጠሪያ ሙከራ”** ማለት በፍቱንነት ሙከራ በሚካሄድበት መደብ አቅራቢያ ወይም አጠገብ ፀረ ተባይ ሳይደረግበት የአከባቢውን ስነ ምህዳራዊ ሁኔታ ወጥነት ለማነጻጸር ጥቅም ላይ የሚውል የሙከራ ነው፤

16) **“ውስን ጠቀሜታ ያለው ፀረ ተባይ”** ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ዝቅተኛ ለሆነ ሰብል ወይም በተከለለ አካባቢ እና ለውስን አገልግሎት

የሚለማ ሰብልን ተባይ ለመከላከል ወይንም ለማንኛውም ለተገደበ እና ውስን ለሆነ አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ፀረ ተባይ ነው፤

17)**“ማነጻጸሪያ ፀረ-ተባይ”** ማለት ለምዝገባ የሚቀረበው ፀረ-ተባይ በፍቱንነት ሙከራ ጊዜ የሚወዳደርበት ፀረ ተባይ ነው፤

18)**“የሙከራ ፕሮቶኮል”** በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚዘጋጅ እና የፀረ ተባይ ፍቱንነትን ለመሞከር ባለሞያው ወይም ተመራማሪው መከተል ያለበት የሙከራ ቅደም ተከተል ነው፤

19)**“የዋና መመዘኛ ነጥብ”** ማለት የፀረ ተባዩን ፍቱንነት ለመመዘን በቅድሚያ ጥቅም ላይ የሚውል የመመዘኛ ነጥብ ነው፤

20)**“መለስተኛ የመመዘኛ ነጥብ”** ማለት የፀረ ተባዩን ፍቱንነት ለመመዘን ከዋና መመዘኛ ነጥብ በተጨማሪነት እና አጋዥነት ጥቅም ላይ የሚውል ነጥብ ነው፤

21)**“ኦ.ኢ.ሲ.ዲ”** ማለት የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት ነው፤

22)**“እውቅና ያለው ቤተሙከራ”** ማለት የ ኦ.ኢ.ሲ.ዲ መርህን መሰረት ያደረገ እና አለምአቀፍ እውቅና ካለው አካል የተሰጠ የመልካም ላቦራቶሪ አተገባበር ምስክር ወረቀት ያለው ቤተሙከራ ወይንም ቤተሙከራው ባለበት ሀገር መንግስታዊ ተቋም የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ያለው ቤተ ሙከራ ነው፤

23)**“ባች”** ማለት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተመረተ የፀረ ተባይ ምርት ስብስብ ነው፤

24)**“የምርመራ የምስክር ወረቀት”** ማለት ፀረ ተባይ ምርት ላይ ናሙና በመውሰድ ፀረ ተባዩ በምርት ወቅት ያለውን ይዘት ለማወቅ የሚረዳ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤትን የያዘ የምስክር ወረቀት ነው፤

25)**“ዝቅተኛ ስጋት ያለው ፀረ ተባይ”** ማለት በሰው እና በአካባቢ ላይ የሚያደርስው የጎንዮሽ ጉዳት ዝቅተኛ የሆነ እና ፍቱንነቱ የተረጋገጠ ፀረ ተባይ ነው፤

26)**“የቁስ ደህንነት አያያዝ ደህንነት መረጃ”** ማለት  የፀረ ተባዩን ኬሚካላዊ ይዘትን ፣ በሰው እና በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ ከድንገተኛ አደጋ ጋር በተያያዘ መታወቅ ያለበትን እና መደረግ ያለበትን ነገር ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ ነው፤

27)**“ፀረ ተባይ ምርት መለያ”** ማለት በአምራች ወይም በአዘጋጅ የሚዘጋጅ እና ፀረ ተባይ ጥቅም ላይ ለመዋል የመጨረሻው ትንሹ ማሸጊያ ላይ ተለጠፎ መሰረታዊ የአጠቃቀም እና የደህንነት መረጃ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

28)**“በራሪ ወረቀት ማለት”** ማለት በአምራች ወይም በአዘጋጅ የሚዘጋጅ እና በምርት መለያ ሰነድ ላይ በቦታ ጥበት ምክንያት ያልተገለፀ የፀረ ተባዩ አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ ጥንቃቄ፣ አያያዝ ፣ አወጋገድ የመሳሰለ መረጃን የያዘ ወረቀት ነው፤

29)**“የአጠቃቀም መመሪያ ሰነድ”** ማለት የፀረ ተባዩን ቴኪኒካል ይዘት እና አጠቃቀም መመሪያን የያዘ እና የፀረ ተባይ ባለሙያ፣ የግብርና ተመራማሪ፣ የኬሚስትሪ ባለሙያ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ወዘት መረዳት በሚችሉት ልክ ዝርዝር መረጃን የያዘ ሰነድ ነው፤

30)**“አስተዳደራዊ ሰነዶች”** ማለት ለምዝገባ ከቀረበው ፀረ ተባይ ጋር በተየያዘ የባለቤትነት ፣ የውክልና ፣ የመልካም አመራረት ልምምድ የመሳሰሉትን የሚያካትት ሰነድ ነው፤

31)**“የሙከራ ምርምር እቅድ”** ማለት ባለስልጣኑ ያወጣውን የሙከራ ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ፈቃድ በተሰጠው ተመራማሪ የሚዘጋጅ የፀረ ተባይ ፍቱንነት ሙከራ የምርም ዕቅድ ነው፤

32)**"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማለት ነው፤

33) **"አዋጅ "**ማለት የፀረተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 674/2010 ነው፤

34) በአዋጅ የግብርና ባለስልጣንን ስልጣንና አደረጃጀት ለመወሰን በወጣው በደንብ ቁጥር 509 አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ በሚመረት ወይም በሚዘጋጅ እና ከውጭ አገር ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባ ፀረ-ተባይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፀረ ተባይ ምዝገባ ሂደት

**4. ስለምዝገባ**

ባለስልጣኑ ፡-

1) የፀረ-ተባይ ምዝገባ አገልግሎት ስራ በድህረ-ገፅ የሚከናወን ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ መረጃው በአመልካች አማካኝነት በግንባር እንዲቀርብ ሊደረግ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የቀረበውን መረጃ ላይ ባለስልጣኑ ቅድመ ግምገማ ማከናወን አለበት፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት በተደረገ ቅድመ ግምገማ መረጃው ተቀባይነት ካገኘ በፀረተባዩ ላይ የቴክኒክ ግምገማ እንዲከናወን ያደርጋል፤

4) የሚቀርብ ማመልከቻን እንደአመጣጥ ቅደም ተከተል የሚያስተናግድ ሲሆን የአዲስ ግኝት የሆነ ፀረ-ተባይን ወይም በሰው ወይም በአካባቢ ላይ ዝቅተኛ ስጋት ያለው ፀረ ተባይን ወይም የተለየ አጠቃቀም ያለው ፀረ ተባይን ወይም አስፈላጊነቱን እና ጠቀሜታው ተሳቢ በማድረግ በራሱ አነሳሽነት እንዲመዘገብ የሚፈልገው ፀረ ተባይ በዚህ መመሪያ የተገለፀውን ሁኔታ ሲያሟላ በቅድሚያ ወይንም እንዳስፈላጊነቱ በፈጠነ መንገድ እንዲስተናገድ ሊያደርግ ይችላል፤

5) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርቡ መረጃዎችን ታዓማኒነትን ለማረጋገጥ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን አባሪ 1 ቅፅ በአስመዝጋቢው እንዲሞላ ማድረግ አለበት፡፡

**5. ውስን ጠቀሜታ ያለው ፀረ-ተባይ**

ውስን ጠቀሜታ ያለው ፀረ-ተባይ ሊመዘገብ የሚችለው፡-

1) ፀረ-ተባዩ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያግዝ የደህንነት መጠበቂያ ቁስ ከምርቱ ጋር አብሮ የሚቀርብ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

2) የተሟላ የፀረ-ተባይ ደህንነት መረጃ ሲኖረው፣

3) በአምራች አገር የተመዘገበና በአለም የምግብና እርሻ ድርጅት ወይም በአለም የጤና ድርጅት የሚወጡትን ውስን ጠቀሜታ ያለው ፀረ ተባይ ቁጥጥር መመሪያ መስፈርትን ሲያሟላ ነው፡፡

**6. ዝቅተኛ ስጋት ያለው ፀረ-ተባይ**

ዝቅተኛ ስጋት ያለው ፀረ-ተባይ ሊመዘገብ የሚችለው፡-

1) ፀረ-ተባዩ በተመረተበት አገር የተመዘገበና በአለም የምግብና እርሻ ድርጅት ወይም በአለም የጤና ድርጅት የወጣውን የዝቅተኛ ስጋት ፀረ ተባይ ቁጥጥር መመሪያን መስፈርትን ያሟላ ሲሆን እና፤

2) አምራቹ ዝቅተኛ ስጋት ያለው ፀረ-ተባይ ስለመሆኑ የተሟላ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ነው፡፡

**7. ቅደመ ግምገማ ስለማካሄድ**

1) በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት መረጃ ሲቀርብለት ባለስልጣኑ ፀረ-ተባዩን አስመልክቶ የሚከተሉት ስለመሟላታቸው ቅደመ ግምገማ ያከናውናል፡-

ሀ) ፀረ ተባዩን ወይም ፀረ ተባዩ የተዘጋጀበትን ንጥረ ነገር አካላዊ እና ውህዳዊ ባህሪን የተመለከተ ጥናት፣

ለ) ዓለማቀፍ ስምምነትን ፣

ሐ) የሰው ጤና ቶክሲኮሎጂ ጋር የተያያዘ ጥናትን ፤

መ) የአካባቢ ቶክሲኮሎጂ ጋር የተያያዘ ጥናትን፤

ሠ) የሀገር ውስጥ ፍቱንነት ሙከራ ውጤትን፤

ረ) አስተዳደራዊ ሰነድን

ሰ) የማስወገጃ ዘዴዎች ሰነድን፣

ሸ) የመጀመሪያ ዕርዳታና የመመረዝ ሕክምና መረጃን፤

ቀ) መለያ እና በራሪ ጽሁፍን፤

በ) የማዘጋጃው ወይም ማምረቻው መግለጫ እና የማምረት ፍቃድን፤,

ተ) በባለስልጣኑ የተሰጠ የመልካም አመራረት ልምምድ የምስክር ወረቀትን፣

ቸ) የፀረ-ተባይ ዝግጅቱ የይዘት ምርመራ ትንታኔ ሰርተፊኬትን፤

ነ) ከአቀማመጥ ጋር ወይም ክምችት ጋር የተያያዘ ጥናትን፤

ኘ) በአምራቹ ወይም በአዘጋጁ እና በሀገር ውስጥ ወኪሉ መካከል የተደረገ የውክልና ስምምነት ሰነድን፣

አ) ፀረ-ተባዩ በሚመረትበት ወይም በሚዘጋጅበት ሀገር የተመዘገበ ስለመሆኑ መረጃ፤

2) የቅደመ ግምገማውን ያለፈ ፀረ ተባይ ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ የሚደረግለት ሲሆን ቅደመ ግምገማውን ያላለፈ ፀረ ተባይ በ10 ተከታታይ ቀናት የጎደለወን መረጃ ወይም ሰነድ እስኪያሟላ ይጠበቃል፤በተጠቀሰው ጊዜ መረጃው ወይም ሰነዱ ካልተሟላ የቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ይደረጋል።

## 8. ስለ ቴክኒክ ግምገማ

ባለስልጣኑ ማንኛውም ፀረ-ተባይ ከመመዝገቡ በፊት የፀረተባዩን አካላዊና ውህዳዊ ባህሪ ፣ የሰው ጤና ቶክሲኮሎጂ እና የአካባቢ ቶክሲኮሎጂ ስጋትን የተመለከተ ጥናት፤ ፀረተባዩን የተመለከተ የደህንነት መረጃን፣የፀረ-ተባይ ዝግጅቱ የይዘት ምርመራ የምስክር ወረቀት እና የፍቱንነት ምርምር ውጤትላይ የቴክኒክ ግምገማ ማድረግ አለበት።

## 9. የፀረ ተባዩ አካላዊና ውህዳዊ ባህሪ መረጃ ቴክኒክ ግምገማ

ባለስልጣኑ በአባሪ 2 በቀረበው መረጃ መሰረት የፀረ ተባዩ አካላዊ እና ውህዳዊ ባህሪን አስመልክቶ የሚከተሉት ላይ የቴክኒክ ግምገማ ማከናወን አለበት፡-

1) የፀረ-ተባዩ የወል ስም ፣የንጥረ ነገር ሳይንሳዊ ስም እና የንጥረ ነገር አሰራር ማበልጸጊያ ልዩ መለያን በተመለከተ ፤

2) የኬሚካል ምድብ ፣ ኬሚካላዊ ቀመርና ቅርጽ እና የተዘጋጀ ምርት ስምን በተመለከተ ፣

3) የዋና ንጥረ ነገር እና የተዘጋጀ ምርት ቅድመ ተከተላዊ የአሰራር ዘዴ ትንታኔን በተመለከተ ፣

4) የዋና ንጥረ ነገር እና የተዘጋጀ ምርት የፊዚካልና ኬሚካል ባህሪን የተመለከተ እውቅና ባለው ቤተ-ሙከራ የተሰራ የአምስት ዙር ውጤት መግለጫ የምስክር ወረቀት ስለመኖሩ ፣

5) በከፍተኛ እና በዝቅተኛ የሙቀት መጠን የንጥረ ነገር ይዘት ፅናት በ54°ሴ እና 0°ሴ መካከል ስለመሆኑ፤

6) የምርቱን መጠነ-ቁሱ፣ ጥቅል መጠነ-ቁስ፤ ከሌላ ፀረ-ተባይ ጋር ያለው መስተጋብር እና ሳይበላሽ የሚቆይበት ጊዜ በተመለከተ ፤

7) የሀይድሮጅን አዮን ልኬት፤ የአሲዳማነት ወይም ቤዛማነት ባህሪያትን ስለማካተቱ፣

8) የቅሪት መጠኑን ለመለካት የዋለውን የምርመራ ዘዴ ፣

9) የማንኛውም ፀረ-ተባይ የዝግጅት ምርት የአገልግሎት ዘመን ከሁለት አመት የሚበልጥ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ እውቅና ባለው አካል የተሰራ የሙከራ ሪፖርትና የውጤት መግለጫ የምስክር ወረቀት ያለው ስለመሆኑ ፣

10) በባለስልጣኑ ቤተ-ሙከራዎች ወይንም ባለስልጣኑ በሚሰይማቸው ተቋማት የዝግጅት ምርት የፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ባህሪያት ሚገልጽ ሪፖርትና የውጤት መግለጫ የምስክር ወረቀት ያለው ስለመሆኑ፡፡

10. **ከሰው ጤና ቶክሲኮሎጂ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የቴክኒክ ግምገማ**

ባለስልጣኑ በአባሪ 3 በቀረበው መረጃ መሰረት ፀረ-ተባዩ ከሰው ጤና ቶክሲኮሎጂ ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን የቴክኒክ ግምገማ ማከናወን አለበት፡-

1) የጥናት ውጤቱ በሙሉ የኦ.ኢ.ሲ.ዲ መመሪያ መሰረት የተሰራና ጥሩ ቤተሙከራ ልምምድ መርሆን የተከተለ ወይም ሙከራው በተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተ-ሙከራ የተሰራ ስለመሆኑ፣

2) በፀረተባዩ ምክንያት ወዲያውኑ ስለሚከሰት የመመረዝ ጉዳትን በተመለከተ በዓይጥ፣ በጥንቸልና በጊኒ አሳማ ላይ ስለመሰራቱ፣

3) በፀረ-ተባዩ አማካኝነት ሊመጣ የሚችል የአጭርና የረጅም ጊዜ መመረዝን፣ በካንሰር የሚመጣ ጉዳትን፣ በነርቭ ስርዓት ላይ የሚደርስ ጉዳትን፣ በጽንስ ላይ የሚደርስ ጉዳትን፣ በዘረመል ላይ እና በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ስለሚያደርሰው ተጽእኖ፣

4) የፀረ-ተባዩ የቅሪት ምርመራ ሙከራ ውጤት እንዲሁም ከሰብል መሰብሰብ በፊት መቆየት ያለበትን ጊዜ በተመለከተ በባለስልጣኑ ቤተ-ሙከራ ወይም ባለስልጣኑ በሚሰይመው ተቋም የተሰራ የቅሪት-ሙከራ ጥናት ሰነድ ስለመኖሩ፡፡

11. **ከአካባቢ ቶክሲኮሎጂ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የቴክኒክ ግምገማ**

ባለስልጣኑ በአባሪ 4 በቀረበው መረጃ መሰረት ፀረ-ተባዩ ከአከባቢ ጋር በተያያዘ ሰላለው ቶክሲኮሎጂ በተመለከተ በሚከተሉት ላይ የቴክኒክ ግምገማ ማከናወን አለበት፡-

1) ፀረተባዩን በተመለከተ በሁለት የአሳ ዝርያ፣ በሁለት የወፍ ዝርያ ፣ በዳፊኒያ፣ በንብ፣ በአልጌ፣ በአፈር ደቂቀ ህዋሳት ላይ በተሰራ የቶክሲኮሎጂ ጥናት ፤

2) ፀረ-ተባዩ በአፈርና በውሀ ውስጥ የሚኖረው ባሀሪ ፤የፀረ-ተባዩ የመቀየር ሂደት እና በፀረ-ተባዩ መቀየር ሂደት የሚፈጠር ንጥረ ነገር እና ባህሪውን በተመለከተ ጥናት ፤

3) ፀረ-ተባዩ አገልግሎት ላይ በሚውልበት ወቅት ተባዩን ለመቆጣጠር የሚችልበትን መንገድ በተመለከተ በተደረገ የማጠቃለያ ጥናት፡፡

**12. የፀረ-ተባይ የደህንነት መረጃ ሰነድ ላይ የሚደረግ የቴክኒክ ግምገማ**

ማንኛውም የፀረ-ተባይ የደህንነት መረጃ ሰነድ ቢያንስ የሚከተለውን ማካተት ይኖርበታል፡-

1) የፀረ-ተባዩን የዝግጅትና የንጥረ ነገር ስም፣
2) የፀረ-ተባዩን ዝግጅት ይዘት፣
3) ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ባሕሪ፣
4) ፀረ-ተባዩ የሚሰጠው አገልግሎት በጤናና በአካባቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት፣
5) በድንገተኛ መመረዝ ወይንም ለፀረ-ተባዩ በመጋለጥ ምክንያት የሚደርስ አደጋን ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃን፤
6) በእሳት አደጋ ወይንም በድንገተኛ የፀረ-ተባዩ ፍሳሽ ምክንያት የሚደርስ አደጋን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃን፡፡

**13. የተዘጋጀው ፀረ-ተባይ ይዘት ላይ የሚደረግ የቴክኒክ ግምገማምርመራ የምስክር ወረቀት**

1) የተዘጋጀው ፀረ-ተባይ ይዘት ምርመራ ምስክር ወረቀት የሚከተለውን ዝርዝር ሊያሟላ ይገባል፡-

ሀ) የአምራች ስም፣

ለ) የናሙና መለያ፣

ሐ) ናሙና የተወሰደበት ቀን፣

መ) ሙከራው የተሰራበት ቀን፣

ሠ) ሙከራውን የተሠራበት ቤተ-ሙከራ ስም፣

ረ) ሙከራውን ያከናወነው የባለሙያ እና የስራ ሀላፊ ስምና ፊርማ፣

ሸ) የፀረ-ተባዩ ቀለም፣

ቀ) አካላዊ ሁኔታ፣

በ) መጠነ-ቁስ፤ የዋናው ንጥረ ነገር መጠን በመቶኛ፣

ተ) የአብራዥ አይነትና መጠን በመቶኛ፣

ቸ) የማሟያ ቁስ አካላት አይነትና መጠን በመቶኛ ፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሰውን የውጤት መግለጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ቤተ-ሙከራ ሙከራውን ለማከናውን ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፡፡

14. **ስለፀረ ተባይ ፍቱንነት ሙከራ**

1) የፀረ ተባይ ፍቱንነት ግምገማ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ወይም ተከታይ የመረጃ ምንጭ መሰረት አድርጎ የሚከናወን ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ባለስልጣኑ አስመዝጋቢውን ወይም አምራቹን ወይም ተመራማሪውን ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይችላል፡፡

2) ማንኛውም በምዝገባ ወቅት የሚቀርብ በሀገር ውስጥ የተሰራ የፀረ ተባይ ፍቱንነት ሙከራ ውጤት ተቀባይነት የሚኖረው ከባለስልጣኑ አስቀድሞ በሚገኝ ፈቃድ መሰረት የተሰራ ከሆነ ብቻ ነው፤

3) የፍቱንነት ሙከራ ለማሰራት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተብሎ አባሪ 5 መሰረት የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት ፣`በአምራቹ የሚዘጋጅ ምርት አያያዝ ደህንነት ሰነድ እና የአጠቃቀም መመሪያ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል፤

4) ባለስልጣኑ ማንኛውም የፍቱንነት ሙከራን ለማከናወን የሚቀርብ ናሙና ከአምራቹ መላኩን በማረጋገጥ ናሙናው ምርምር ወደ ሚደረግበት ተቋም እስኪደረስ ያለውን ሂደት ክትትል ማድረግ አለበት፤

5) አስመዝጋቢው የናሙና ማስገቢያ ፈቃድ ለመጠየቅ በአባሪ 6 መሰረት የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት ከምርምር ተቋሙ ጋር የተደረገ መግባባያ ስምምነት ሰነድ እና በተመራማሪው የሚዘጋጅ የሙከራ ምርምር ዕቅድ ማቅረብ የኖርበታል፤

6) እያንዳንዱ አስመዝጋቢ ምዝገባ ለሚጠይቅበት ፀረ-ተባይ ለማነጻፀሪያ የሚሆን የዋናው ንጥረ ነገር ትንታኒያዊ ማነጻፀሪያ ናሙና ማቅረብ አለበት፤

7) ማንኛውም ፀረ ተባይ በሙከራ ላይ እያለ የምረምር ዕቅዱን መሰረት በማድረግ በባለስልጣኑ ሰራተኞች የመስክ ምዝገባ ይደረጋል፤

8) ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ በማነጻጸሪያነት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛወም ፀረ ተባይ ተቀባይነት አይኖረውም፤

9) ማንኛውም የምርምር ተቋም ወይም ተመራማሪ ሙከራን የሚያከናውነው ባለስልጣኑ የሚያወጣውን የሙከራ መመሪያ መሰረት አድርጎ መሆን ይኖርበታል ፡፡

15. **ቀዳሚ የመረጃ ምንጭን በመጠቀም የሚደረግ የፀረ ተባይ ፍቱንነት ግምገማ**

ቀዳሚ የመረጃ ምንጭን በመጠቀም የፀረ ተባይ ፍቱንነት ግምገማ የሚከናወነው፡-

1) የፀረ ተባዩ አምራች ወይም የሚያመርትበት ቦታ አዲስ ከሆነ፣

2) የፀረ ተባዩ ንጥረ ነገር አዲስ ከሆነ ወይም ከዚህ ቀደም ሀገር ውስጥ ጥቅም ያልዋለ ከሆነ፣

3) የንጥረ ነገር ይዘት መጠኑ ከተቀያየረ፣

4) ከሌላ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ንጥረ ነገር ጋር ተዋህዶ የተዘጋጀ ከሆነ

5) በአዲስ ሰብል ወይም አዲስ የተባይ አይነት ላይ ምዝገባ የተጠየቀበት ከሆነ ነው።

**16. ተከታይ የመረጃ ምንጭን በመጠቀም የሚደረግ የፀረ ተባይ ፍቱንነት ግምገማ**

ተከታይ የመረጃ ምንጭን በመጠቀም የፀረ ተባይ ፍቱንነት ግምገማ የሚከናወነው፡-

1) የፀረ ተባዩ ንጥረ ነገር ከአንድ በላይ ሰብል ወይም ተባይ ዓይነት በላይ መቆጣጠር እንደሚችል አሳማኝ መረጃ ካለው፤

2) ተቀራራቢ ስነ ህይወታዊ ትስስር እና ዝምድና ላላቸው ሰብል ወይም ተባይ አይነቶች መቆጣጠር እንደሚችል በሳይንሳዊ መረጃ የተረጋገጠ ከሆነ፤

3) በአነስተኛ መጠን በውስን ቦታ ለሚመረቱ የሰብል ዓይነቶች ብቻ አገልግሎት ላይ እንደሚውል ከተረጋገጠ፤

4) ባለስልጣኑ በተለያዩ ምክንያቶች የፀረ ተባዩን ንጥረ ነገር ጥቅም ላይ መዋል አስቸኳይ መሆኑን ካመነበት።

**17. ስለ ፍቱንነት ግምገማ መመዘኛ ነጥብ**

1) በፍቱንነት ግምገማ ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ዋና የመመዘኛ ነጥብ ሁነው ያገለግላሉ፡-

ሀ) ምርታማነት፣

ለ) ተባይ የማጥፋት ወይም የመቆጣጠር መጠን በመቶኛ፣

ሐ) ከዒላማ ውጪ በሆነ እፅዋት ላይ ያለ የጎንዮሽ ጉዳት፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች መለስተኛ የመመዘኛ ነጥብ ሆነው ያገለግላሉ

   ሀ) ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ፣

   ለ) ለተቀናጀ ተባይ መከላከል ያለው አስተዋፆ

   ሐ) ተባይ የመላመድ ሁኔታ ፤

3) በዋና መመዘኛ ነጥብ አዎንታዊ ውጤት ያገኘ ፀረ-ተባይ በመለስተኛ መመዘኛ ነጥብ ዝቅተኛ ውጤት ካገኘ ፀረ ተባዩ ከጥብቅ የአጠቃቀም መመሪያ እና ቅድመ ሁኔታ ጋር እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

## 18. ስለ ፍቱንነት ሙከራ ውጤት ተቀባይነት ማጣት

የፀረተባይ የፍቱንነት ሙከራ ውጤት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፡-

1) ለምዝገባ የቀረበው ፀረ-ተባይ በሰብል ምርታማነት እና ተባይ የማጥፋት ወይም መቆጣጠር ላይ ያለው አዎንታዊ ተፅኖ ከመቆጣጠሪያ ሙከራ በስታቲስቲክስ ጉልህ ከሆነ፣

2) ለማነጻጸሪያነት የቀረበው ፀረ ተባይ ወይም የተባይ ማጥፊያ ዘዴ ጋር በስታቲስቲክስ እኩል ወይም የተሻለ አዎንታዊ ተፅኖ ካለው፣

3) ፀረተባዩ በታለመለት ሰብል፣ አቅራቢያ ሰብል እና ተከታይ ሰብል ላይ ያለው አሉታዊ ተፅኖ ከማነጻጸሪያው በስታቲስቲክስ በጉልህ ያነሰ ከሆነ፣

4) በአስመዝጋቢው እና በምርምር ተቋሙ ወይም ተመራማሪው መካከል የጥቅም ግንኙነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

5) የፀረተባዩ የፍቱንነት ሙከራ ውጤቱን በተመለከተ በባለስልጣኑ ባለሞያዎች በመስክ ጉብኝት ወይም ውጤቱ ከወጣ በኂላ ለሚነሳው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ሳይሰጥ ከቀረ ወይም ውጤቱ አሻሚ ከሆነ፣

6) የፀረተባዩ ናሙና ሚስጥራዊ ሰንሰለቱን ጠብቆ ተመራማሪው ጋር ካልደረሰ፤

7) የፀረተባዩ የፍቱንነት ሙከራው ባለስልጣኑ ያወጣውን የሙከራ ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ካልተሰራ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ምዝገባ ውሳኔ ፤ ምዝገባ ዕድሳት እና የምዝገባ ምስክር ወረቀት

### 19. የምዝገባ ውሳኔ

ባለስልጣኑ፡-

1) ምዝገባ ስለተጠየቀበት ፀረ-ተባይ የቀርበ ሰነድንና መረጃን አገራችን ካጸደቀችውና ከተቀበለችው አለም አቀፍ አሰራር መሰረት በማድረግ በቤተ ሙከራ በመፈተሽ የሚገኘውን ውጤት በመተንተን የፀረ-ተባይ ዶዚየር ግምገማ ላይ በመመስረት ምዝገባው ተቀባይነት እንዲያገኝ ወይም ምዝገባው ውድቅ እንዲሆን በባለሙያ የቀረበውን ምክረ ሀሳብ ከግምት በማስገባት የምዝገባ ውሳኔ ይሰጣል፤
2) እንደ አስፈላጊነቱ በአስመዝጋቢው የቀረበውን ሰነድ ከመነጨበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ቀንስላ ወይም ኢምባሲ እንዲረጋገጥ መጠየቅ ይችላል፤
3) ፀረ ተባዩ የቅድመ ግምገማውን እና የቴክኒክ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ እና በአስተዳደራዊ ሰነዶች ተገምግመው በሰው እና በአካባቢ ላይ የጎላ ችግር የማያስከትል እና በፍቱንነቱ የተሻለ መሆኑ ካረጋገጠ ለአምስት አመት የሚቆይየ ምዝገባ ሰርተፊኬት ይሰጠዋል፤
4) ፀረ ተባዩ የቴክኒክ መስፈርቱን ካላሟላ ወይም ፍቱንነት ግምገማው ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በአስተዳደራዊ ሰነዶች ተገምግሞ በሰው ወይምበአካባቢ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅኖ ከጠቀሜታው አንጻር ከፍተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ምዝገባው ውድቅ ያደርጋል፤
5) ፀረ ተባዩ ከአያያዝ፣ ከአጠቃቀም፣ ከአከመቻቸት፣ ከማጓጓዝ፣ ከአወጋገድ ጋር በተያያዘ በተለየ መንገድ የሌሎች ተቋማት ወይም ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ

የሚጠይቅ ከሆነ ለተጨማሪ ግምገማ እና የሚመለከታቸው ባለድርሻዎችን ምክክር ለማድረግ ተጫማሪ ከ ስድስት ወር ያልበለጠ ጊዜ ቀጠሮ የሚሰጠው ሲሆን በጊዜ ቀጠሮ ውስጥ የሚኖረው ውሳኔ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (3) እና በንዑስ አንቀጽ (4) በተገለፁት አግባብ መሰረት እንዲስተናገድ ያደርጋል፤

6) ፀረ ተባዩ  አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅኖው ከፍተኛ ከሆነ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ ተጥሎበት እንዲመዘብ ያደርጋል፤

7) በምዝገባ ሂደት ያልተሟሉ እና የምዝገባውን ጠቅላላ ውጤት የማይወስኑ መስፈርትን ወይም ሰነድን ለሚሟላት ለአንድ አመት ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ ምዝገባ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

20. **የምዝገባ ምስክር ወረቀት**

1) ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ፀረ ተባዩ እንዲመዘገብ ውሳኔ ከሰጠ የአገልግሎት ክፍያን መጠናቀቁ በማረጋገጥ ለአስመዝጋቢ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

2) የፀረተባይ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚከተለውን መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የፀረ ተባዩ የንግድ ስም ፤

ለ) የወል ስም፤

ሐ) የዋና ንጥረ-ነገር መጠንና ዝግጅት፤

መ) የምርቱ አለምአቀፍ መለያ ቁጥር፤

ሠ) የአስመዝጋቢው እና የመጀመሪያ አስመዚጋቢው ወኪል ስምና አድራሻ፤

ረ) የተመዘገበበት ጥቅም፣ ሁኔታና ገደብ፤

ሰ) ምዝገባው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

ቀ) ፊርማና ቀንን ጨምሮ የ ባለስልጣኑ ህጋዊ ማህተም፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንደ አስፈላጊነቱ የአእምሮአዊ ንብረት ባለቤትነትን የሚገልፅ መረጃ ሊይዝ ይችላል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተደነገገው በተጨማሪ የመጀመሪያው የአስመዝጋቢው ወኪል ስምና አድራሻ እና የፀደቀው መለያና የመያዣ ዝርዝር መረጃ ቅጂ ወረቀት፤ ከምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ጋር አባሪ ተደርጎ ለአስመዝጋቢው ይሰጣል፤

5) የተመዘገበው ፀረ ተባይ ዝርዝር በህትመት ውጤት፣ በመረጃ ቋት፣ በባለስልጣኑ ድሕረ-ገፅ በማስፈር ለተጠቃሚ ህብረተሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

6) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጠውን ስርዓት ተከትሎ አመልካቹ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማሻሻያ ወይም እንደገና ምዝገባ ካልጠየቀና የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ካልተሰጠው በስተቀር በምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ በቀረበ መረጃና ላይ ምንም አይነት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም።

## 21. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

1) አመልካች የምዝገባ ጊዜው ከመጠናቀቁ 90 ቀን በፊት በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የምዝገባ ዕደሳት መጠየቅ ይችላል፤

2) ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ከግምት በማስገባት የምዝገባ ዕድሳት ያከናውናል፡-

ሀ) በቅፁ ተሞልቶ የቀረበው መረጃ ትክክለኛነቱና አግባብነቱ በማረጋገጥና፣

ለ) በድህረ ምዝገባ ዳሰሳ ወቅት ፀረተባዩን አስመልክቶ ከውጤታማነት ፣ከጥራት እና ደህንነት እና ከህገ-ወጥ ስራ ጋር በተያያዘ አንፃር በሰነድ የተደገፈ ቅሬታ ያልቀረበበት መሆኑን፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) ላይ የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፀረ ተባይ የምዝገባው ጊዜ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ካልዋለ የምዝገባ እድሳት ለማግኘት የአገር ውስጥ የፍቱንነት እና የቅሪት ምርመራ ሙከራ በማካሄድ የምዝገባ ዕድሳት እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ በተደነገገው የግዜ ገደብ ያለቀረበ የምዝገባ ዕድሳት ተቀባይነት የለውም ፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የቀረበውን የፀረ-ተባይ ምዝገባ ዕድሳት ጥያቄ ባለስልጣኑ ካልተቀበለው ከነምክንያቱ ውሳኔውን በፅሑፍ አመልካቹ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፤

6) አመልካቹ ውሳኔውን ካልተቀበለ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

22. **የምዝገባ ማሻሻያ**

1) አመልካች የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ የምዝገባ ማሻሻያ ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) በመለያ ወረቀት ላይ ወይም መያዣ ላይ የሚደረግ አነስተኛ ማሻሻያ፤

ለ) አድራሻና ግላዊ መረጃን ጨምሮ የአስመዝጋቢው መረጃ ለውጥ ፤

ሐ) ከፀረ-ተባዩ ጋር የተያያዙ ስጋቶችንና ጥቅሙ ላይ መሻሻል የማያስከትል ከሆነ፤

2) የተጠየቀው ማሻሻያ የሚከተሉት ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን በመገምገም የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፦
   ሀ) በፀረ-ተባዩ ላይ ወይም በአጠቃቀሙ ላይ ለውጥ የማያመጣ ሲሆን፤
   ለ) ከፀረ-ተባዩ ጋር የተያያዘ ፍቱንነትን ወይም የጤና እና የአከባቢ ስጋት ወይንም መርዛማነት የማይለወጥ ሲሆን፤
   ሐ) የፀረ-ተባዩን ህጋዊነት ወይም የመለያ ወረቀቱን ይዘት የማይፃረር ሲሆን እና
   መ) የአስተሻሸጉን አያያዝ ምቹነት ወይም ተያያዥ ስጋቶችን የማይፃረር ከሆነ፤
3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የቀረበውን የፀረ-ተባይ ምዝገባ የማሻሻል ጥያቄ ባለስልጣኑ ካልተቀበለው ከነምክንያቱ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ አመልካቹ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፤
4) አመልካቹ ውሳኔውን ካልተቀበለ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

23. **ዳግም ምዝገባ**

1) በአስመዝጋቢው የቀረበው የዳግም ምዝገባ ጥያቄ የንግድ ስምን ለመቀየር ከሆነ ከማመልከቻው ጋር የቀረበውን ሰነድ ከመነጨበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ቆንስላ ወይም ኢምባሲ የተረጋገጠ ሰነድ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

2) በአስመዝጋቢው የቀረበው የዳግም ምዝገባ ጥያቄ የፀረተባዩን የዋናውን ንጥረ ነገር የቅልቅል መጠን ለመለወጥ ወይም የፀረተባዩን አጠቃቀሙን ለመለወጥ ከሆነ አዲስ

የፍቱንነት ወይም የቶክሲኮሎጂ ወይም የአከባቢ ቶክሲኮሎጂ ወይም የቅሪት ወይም የጥራት ጥናት ውጤት ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

3) የዳግም ምዝገባ ጥያቄ የቀረበው ፀረተባዩን ያስመዘገበው ሰው በሌላ ሰው መቀየር ተፈልጎ ከሆነ ከማመልከቻው ጋር የቀረበውን ሰነድ ከመነጨበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ቆንስላ ወይም ኢምባሲ የተረጋገጠበጥ ሰነድ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

4) ባለስልጣኑ የዳግም ምዝገባ ጥያቄ በቀረበ ከ90 ባልበለጠ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን መስጠት አለበት፤

5) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የተሰጠ ውሳኔ ውሳኔው በተሰጠ በሰባት ተከታታይ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፤

6) በዚህ አንቀፅ መሰረት የቀረበውን የዳግም ምዝገባ ጥያቄ ባለስልጣኑ ካልተቀበለው ከነምክንያቱ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ አመልካቹ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፤

7) አመልካቹ ውሳኔውን ካልተቀበለ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይኖርበታል።

## ክፍል አራት

## ስለ ፀረ ተባይ የንግድ ስያሜ ፤ በራሪ ወረቀት ፤ እና ስለ ሚስጥር አጠባበቅ

### 24. ስለ ፀረ ተባይ የንግድ ስያሜ

የፀረ ተባይ ምዝገባ የሚከናወነው አስመዝጋቢው በሚያወጣው የንግድ ስያሜ እና ምልክት ብቻ ሲሆን የንግድ ስያሜው ወይም መለያው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ምክንያት ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፡-

1) የፀረ ተባይ ንግድ ስያሜ ከህዝብ ሰላም እና ስነ ምግባር ጋር ተጻራሪ በሆነ መንገድ ከተዘጋጀ፤

2) የንግድ ስያሜው በኢኮኖሚያዊ ወይም በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የተለመደ እና በጋራ መግባባቢያ ቋንቋነት የሚያገለግል ከሆነ፤

3) የንግድ ስያሜው ወይም መለያው የፀረ ተባዩን አይነት እና ባህሪ በተመለከተ ህዝቡን ወይም የንግድን ማህበረሰብ የሚያሳስት ከሆነ፤

4) አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ከማንኛውም ሀገረ መንግስት ፣ ከበየነ መንግስታዊ ድርጅት ፣ ወይም በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ከተቋቋመ ሌላ ድርጅት ወታደራዊ ምልክት፣ ሰንደቅ አላማ ወይም ሌላ አርማ፣ ስም፣ ምህጻረ ቃል ወይም አህጽሮተ ስም ወይም በእነዚሁ ከተዘጋጀ ኦፊሴላው ምልከት ወይም የክብር አርማ ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው መለያ ወይም ንግድ ስያሜ ከሆነ፤

5) የሰዎችን ስም የያዘ ንግድ ስያሜ ከሆነ ፤

6) ከአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ፀረ ተባይ ጋር የተያያዘ በሌላ ሰው ወይም ተቋም ቀድሞ የተመዘገበ ፀረ ተባይ ንግድ ስያሜ ወይም መለያ ጋር አንድ የአይነት ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል መልኩ ተመሳሳይነት ያለው ከሆነ ፤

7) የፀረ ተባይ ንግድ ስያሜው ወይም መለያው በሚገባ ከሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የሌላ እቃ ንግድ ስያሜ ወይም መለያ ጋር አንድ አይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ፤

8) በየትኛው መልኩ በኢትዮጵያ ስራ ላይ የዋለውን የንግድ ምልክት ምዝገባ አዋጅ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፡፡

25. **የፀረ-ተባይ ምርት መለያ እና በራሪ ወረቀት**

1) የፀረ-ተባይ ምርት መለያ እና በራሪ ወረቀት በአባሪ 7 መሰረት የተዘጋጀ ሆኖ ፀረ-ተባዩን በተመለከተ የሚከተሉትን መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) አምራች ወይንም አዘጋጁ እና የወኪሉ ስም

ለ) የንግድ ስምና የወል ስም፣

ሐ) የሚቆጣጠረውን የተባይ ዓይነት እና የሰብል ወይም የአጠቃቀም ዓይነት፣

መ) አጠቃቀም፣ የደህንነት ማስጠንቀቂያ፣

ሠ) አጠቃቀም በተመለከተ፣

ረ) የአገልግሎት ማብቂያውን ጊዜ፣

ሰ) ምድባ የሚገልፅ የቀለም መለያና አጠቃቀሙንና ጥንቃቄን የሚገልፅ ስእላዊ መረጃ ፤

2) የሚዘጋጀው የፀረ-ተባዩ መለያ እንግሊዘኛ እና አማርኛ ወይንም በየክልሉ የስራ ቋንቋ እንደሁኔታው መዘጋጀት ይኖርበታል፤

3) በፀረ-ተባይ መያዣ ዕቃ ላይ መደረግ ያለበትን የመለያ ዲዛይን በአባሪ 7 በተገለፀው መልኩ መዘጋጀት አለበት፤

4) የፀረተባይ በራሪ ወረቀት በመለያው ላይ በቦታ ጥበት ምክንያት በበቂ ሁኔታ ያልተገለፀ መረጃንና ሌሎችንም በማካተት ከፀረ-ተባዩ ዶዚየር ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 26. ስለ ሚስጥር አጠባበቅ

1) አመልካቹ በዚህ መመሪያ መሰረት ለምዝገባ የሚያቀርበው መረጃ በምስጢር እንዲጠበቅ ፍላጎት ካለው በምስጢር እንዲጠበቁ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች መለየትና "ምስጢራዊ መረጃ" የሚል ምልክት ማድረግ ይኖርበታል፤

2) የባለቤትነት መብት ጊዜው ላላለቀ ፀረ-ተባይ ከመጀመሪያ ምዝገባ ጀምሮ የባለቤትነት መብቱ እስከሚያልቅ ድረስ የቀረበው መረጃ በሚስጥር መያዝ ይኖርበታል፤

3) ከባለቤትነት መብት ጋር ያልተያያዙ አጠቃላይ መረጃዎች እስከ 10 ዓመታት ድረስ በሚስጥርነት ሊያዝ ይገባል፤

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተገለፁት ጊዜያት ውስጥ ከመጀመሪያው አስመዝጋቢ በፁሑፍ ፍቃደኝነት ካልቀረበ በስተቀር ለሌላ አመልካች መረጃው አይሰጥም፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፀረ-ተባዩን በተመለከተ ባለስልጣኑ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጨምሮ ሌሎች ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነበትን መረጃ ግልፅ በሆነ መንገድ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ይችላል፡-

ሀ) የአመልካቹ አድራሻ፤

ለ) የፀረ-ተባዩ መለያ፣ ዋና ንጥረ-ነገር ዝግጅት፤ የዋና ንጥረ- ነገር መጠንና ከፀረ-ተባዩ መርዛማነት ወይም ከአካባቢ አንፃር አሳሳቢ የሆኑ የሚጨመሩ ተጨማሪ መቀላቀያዎችን የሚገልፅ ፤

ሐ) የታለመለትን ጥቅም፤

መ) መርዛማነቱንና በአካባቢ ላይ ያለው ተፅእኖ፤

ሠ) በሰብልና በአካባቢ ላይ ያለው ባህሪና እጣ ፈንታ፤

ረ) ሊያደርስ የሚችለው አካላዊ ጉዳት፤

ሰ) የማስወገጃ ዘዴዎች፤

ሸ) የመመረዝ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ፤

6) በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀረበው ዶሴር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው የህዝብ ፍላጐት ሲኖር እና በአመልካቹ ጥያቄ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን መረጃዎች ለህብረተሰቡ ግልጽ ሊያወጣ ይችላል፡-

ሀ) የፀረ ተባዩን የዝግጅት ዝርዝር፤

ለ) የአመራረት ሂደት፤

ሐ) በዋናው ንጥረ ነገር ውስጥ የሚገኝ ያልተጣራ ኬሚካል ዝርዝር፣

መ) በዋናው ንጥረ ነገር ውስጥ የሚገኝ ያልተጣራ ኬሚካል የምርመራ ዘዴ፤

ሠ) በዋናው ንጥረ-ነገር ውስጥ የሚገኝ አላስፈላጊ ኬሚካልን ጨምሮ የዋናው ንጥረ-ነገር የያንዳንዱ የምርት ዘውግ ወይም ባች የምርመራ ውጤት፤

ረ) በአምራቹ ወይም በአዘጋጁ ና በአመልካቹ ወይም በአስመዝጋቢው ወኪል መካከል ያለ የግንኙነት መረጃ፤

ሰ) ፀረ-ተባዩ የጀርባ አጥንት ባላው እንስሳት ላይ ያለውን ተጽእኖ ሙከራ ያካሄዱት ሰዎች ስምና አድራሻ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

**27. ክልከላ**

1) ከአንድ አምራች ወይም አዘጋጅ በተመሳሳይ አዘገጃጀት የተመረተን ምርት በተለያየ የንግድ ስም ማስመዝገብ የተከለከለ ነው፤

2) የክልከላ ውሳኔ የተሰጠው አመልካች ውሳኔውን በተመለከተ በ60 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በወጣ የቅሬታ ማቅረቢያ ድንጋጌዎች ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**28. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌ***

*ይህ መመሪያ* ከመውጣቱ በፊት የዚህን *መመሪያ* ድንጋጌዎች በሚቃረን መልኩ የተከናወኑ የፀረተባይ ምዝገባዎች ይህ *መመሪያ* ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ምዝገባ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

**29. *መመሪያው* የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ *መመሪያ* በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጹ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 10 ቀን 2017 ዓ.ም.

ግርማ አመንቴ (ፒኤችዲ)

የግብርና ሚኒስቴር

ሚኒስትር

**አባሪ 1 የፀረ-ተባይ ቅድመ ግምገማ ማመልከቻ ቅጽ**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አዲስ ንጥረ ነገር የያዘ ፀረ-ተባይ | | |
| | | |
| ለ. ፀረ-ተባይ የዋናው ንጥረ ነገር ወይም ዝግጅቱ ከተመዘገበ ፀረ-ተባይ ጋር ተመሳሳይ ያልሆነ | | |
| | | |
| ሐ. ምዝገባን ማስተላለፍ | | |
| | | |
| መ. ተመዝግቦ ያለን ፀረ-ተባይ የምዝገባ ሁኔታ ማሻሻል | | |
| | | |
| ሠ. ሌላ | | |
| | | |

| 1. **አመልካች** | |
|---|---|
| 1.1 መለያ | የፀረ-ተባዩ አስመዝጋቢ ስም |
| 1.2<br><br>የአመልካቹ የስራ ድርሻ | |
| 1.3<br><br>የቦታ አድራሻ | |
| 1.4<br><br>የፖስታ አድራሻ | |
| 1.5 የቴሌፎን አድራሻ | |
| 1.6<br><br>የፋክስ አድራሻ | |
| 1.7 የኢሜይል አድራሻ | |

| 2. **የፀረ-ተባዩ ዝግጅት** | | |
|---|---|---|
| 2.1 ዲስግኔሽን | የንግድ ስም | |
| | የንግድ ምልክት | |

| | | |
|---|---|---|
| | የንግድ ምልክቱ ባለቤት | |
| 2.2 የፀረ-ተባዩ የመቆጣጠር ስራ | | |
| 2.3 የታለመው አገልግሎት (ለሰው ጤና፣ ለእንስሳት ጤና፣ ለኢንዱስተሪ፣ ለደን ፣ለግብርና ወዘተ | | |
| 2.4: ፀረ-ተባዩ ሚቆጣጠረው ተባይና የሚረጭበት የሰብልዓይነት | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2.5: የመቆጣጠር ዘዴ መጠን እና የርጭት ድግግሞሽ | | | |
| 2.6 የፀረ-ተባዩ ዝግጅት ዓይነት | | | |
| 2.7 አሁን ያለ የምዝገባ ቁጥር | | | |
| 2.8 በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ያለው የምዝገባ ሁኔታ | | | |
| 2.9 በሌሎች ሀገሮች ያለው የምዝገባ ሁኔታ | | | |
| 2.10 የፀረ-ተባዩ ዝግጅት በሚመረትበት ሀገር የተመዘገበ ነውን | ከተመዘገበ ማስረጃ ይቅረብ | | |

| 3. ዋና ንጥረ ነገር | | | |
|---|---|---|---|
| የዋና ንጥረ ነገሮች የወል ስም | አምራች/ስምና አድራሻ/ | ዝቅተኛ ጥራት በመቶ | ልዩነት |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |

| **4. የተዘጋጀ ፀረ-ተባዩ** | |
|---|---|
| 4.1 የአዘጋጅ /ስም/ | አድራሻ |

| 4.2 የፀረ-ተባዩ ይዘት | | | |
|---|---|---|---|
| ቅልቅሎቹና ተግባራቸው | ግራም/በሊትር | ግራም/በኪሎግራ ም | ልዩነት |
| | | | |

**5. ቶክሲኮሎጂ (ዝግጅት ምርት)**

| 5.1 ዓይጥ | አጣዳፊ መመረዝ በአፍ | አጣዳፊ መመረዝ በቆዳ | አጣዳፊ መመረዝ በእስትንፋስ |
|---|---|---|---|
| | በሙከራ የተገኘ | በሙከራ የተገኘ | በሙከራ የተገኘ |

| 5.2 ጥንቸል | የቆዳ መቆጥቆጥ | የዓይን መቆጥቆጥ |
|---|---|---|
| የለም | | |
| መለስተኛ | | |
| መሃከለኛ | | |
| ከባድ | | |

| 5.3 በጊኒ አሳማ የቆዳ ስስነት | የለም | መለስተኛ | መሃከለኛ | ከባድ |
|---|---|---|---|---|

| 5.4 የአለም ጤና ድርጅት የቶክሲኮሎጂ ደረጃ | 1ሀ | 1ለ | II | III | |
|---|---|---|---|---|---|

| |
|---|
| 5.5 የሌሎች አጥቢ እንስሳት መርዛማ ጥናት ማጠቃለያ |
| 5.6 የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ባጭሩ: |
| 5.6.1 ቶክሲኮሎጂ ለንቦች: |
| 5.6.2. ቶክሲኮሎጂ ለአሳ እና ሌሎች የውሃ ፍጥረታት: |
| 5.6.3 መዛማነት ለወፎች: |
| 5.6.4 ቶክሲኮሎጂ ለመሬት ትልና ሌሎች የአፈር ፍጥረታት: |
| 5.6.5 ቶክሲኮሎጂ ለኢ-ኢላማ ፍጥረታት: |
| 5.6.6 በአካባቢ ይ ጸንቶ የመቆየት ሁኔታ |
| 5.6. ሌሎች ተጽእኖዎች: |
| **6. ማሸጊያ** |

| | |
|---|---|
| 6.1 የማሸጊያው እቃ | |
| 6.2 የእሽጉ መጠን | |
| 6.3 ያገለገሉ መያዣዎች አወጋገድ | |

7. መግለጫ

እኔ……………………….በዚህ ማመልከቻ ላይ የሰፈሩት እና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡት መረጃዎች በሙሉ ባለኝ መረዳት እውነት፣ ትክክል እና የተሟሉ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

| | |
|---|---|
| ---------------------------------------------<br>ሙሉ ስም | ---------------------------------------------<br>ፊርማ |
| ቀን | ---------------------------------------------<br>የስራ ድርሻ |
| የአመልካቹ ድርጅት ማሕተም | ለመ/ቤቱ አገልግሎት ---------------<br>አስተያየት ---------------------------------------------<br>---------------------------------------------<br>---------------- ----------------<br>ፊርማ ቀን |

## በአባሪ 2 የፀረ ተባዩ አካላዊ እና ውህዳዊ ባህሪ ዋና ንጥረ-ነገር (ቴክኒካዊ ውጤት)

### 1. መለያ

| | መስፈርች | አስተያየት |
|---|---|---|
| ሀ | የወል ስም | በዚህ መሰረት ይገለፅ |
| ለ | የአምራች የሚስጢር ፅሁፍ | |
| ሐ | ኬሚካላዊ ስም | |
| መ | ኬሚካላዊ ቡድን | |
| ሠ | መዋቅራዊ ቀመር | |
| ረ | መሰረተ ቀመር | |
| ሰ | የፈጠራ ባለቤትነት ሁኔታ | የፈጠራ ባለቤትነት ሁኔታ፡ ምርቱ በፓተንት ስር ከሆነ እና ማመልከቻው የባለቤትነት ባለመብቱ ካልሆነ ፣ ከባለቤትነት ባለመብቱ የተሰጠው የፍቃድ ደብዳቤ በዶሴው ውስጥ መካተት አለበት ። |

›

**አካላዊና ኬሚካላዊ ባህሪይ (ዋና ንጥረ ነገር-ቴክኒካል ደረጃ)**

| | መስፈርቶች | አስተያየት |
|---|---|---|
| ሀ | አካላዊ ሁኔታ | |
| ለ | ቀለም | አግባብነት ያለው ዘዴ / ሙከራ ጥቅም ላይ በሚውልበት እና መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ይሰጣል |
| ሐ | ሽታ | |
| መ | እፍጋት/ጥግግት/መጠነ ቁስ በ 20 ° ሴ | |
| ሠ | የተን/የእንፋሎት ግፊት በ 20/25 ° ሴ | |
| ረ | ኢተለዋጭነት/አይለወጤ የሄነሪ ህግ | |
| ሰ | ውሀዊ ፍርሰት | በውሳኔው ወቅት የሚሰሩትን የሙቀት እና የፒ-ኤች መለኪያዎች በመጥቀስ ገቢር/ዋና ንጥረ ነገር DT 50 (ቀናት) ይስጡ። ጥቅም ላይ የዋለውን ልዩ ዘዴ ያመልክቱ። |
| ሸ | ብርሀናዊ ፍርሰት | |
| ቀ | በውሃ ውስጥ መሟሟት ሁኔታ | በ pH ላይ በውሃ መሟሟት እና ተፅእኖ/ውጤትን ያቅርቡ |
| በ | በካርቦናማ አሟሚዎች ውስጥ የመሟሟት ሁኔታ | መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ያመልክቱ |
| ተ | የውሀ ክፍለት/ክፍልፋይ የፒ-ኤች ውጤት | መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ያመልክቱ |
| ቸ | የፍሌት ነጥብ | መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ያመልክቱ |
| ነ | የቅልጠት ነጥብ | መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ያመልክቱ |
| ኘ | የመሰባበሪያ/የፍርሰት የሙቀት መጠን በ ° ሴ | መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ ያመልክቱ |
| አ | የምርመራ/የትንተና ዘዴ | ሙሉ ማጠቃለያ ዘገባ |

### ለተቀናበረ/የተዘጋጀ ፀረ-ተባይ ምርት ዶሴ

በተገቢው ሰነድ ክፍል ውስጥ ንብረቶችን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋለ በግልጽ የተቀመጠ ዘዴ። የ CIPAC ዘዴዎች ይመከራል ።

| | መስፈርቶች | አስተያየት |
|---|---|---|
| ሀ | አካላዊ ሁኔታ | መግለጫ |
| ለ | ቀለም | |
| ሐ | ሽታ | |
| መ | - ተረጋግቶ የመቀመጥ ሁኔታ/የቆይታ ጊዜ | ለ 14 ቀናት በ 54 ° ሴ ከተከማቸ በኂላ የዝግጅቱን/የቅንብሩን ተረጋግቶ መቆየት ያመልክቱ ። ሌሎች ጊዜዎች እና/ወይም ሌሎች ሙቀቶች (ለምሳሌ 8 ሳምንቶች በ 40 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ፣ 18 ሳምንታት በ 30 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ) ዝግጅቱ የሙቀት ስሜት ያለው ከሆነ በዚህ ሁኔታ ሊቀርብ ይችላል ፣ አዲሶቹ መለኪያዎች መገለጽ አለባቸው ። (ዘዴ እና መጠን/ዋጋ) |
| ሠ | የምርቱ መቆያ ጊዜ | የምርት ሙቀቱ በቤት ሙቀት (30° ሴ) ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በላይ ከሆነ እና ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ በወራት ውስጥ ይሰጣል ። ተገቢው የሙቀት ዝርዝር መግለጫዎች መሰጠት አለባቸው ። |
| ረ | እፍጋት/ጥግግት/መጠነ ቁስ (ፈሳሽ) | የፈሳሾችን እፍጋት/ጥግግት/መጠነ ቁስ (መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ) ያመልክቱ ። |
| ሰ | የውድለት/የጥቅል እፍጋት/ጥግግት/መጠነ ቁስ | ከተጨመቀ በኂላ የጠጣሮችን እፍጋት/ጥግግት/መጠነ ቁስ (መጠን/ዋጋ ሲደመር አሃድ) ያመልክቱ። |
| ሸ | . ከሌሎች ፀረ-ተባዮች ጋር ያለው ተኳሀኘነት/ስምምነት | ሙሉ ማጠቃለያ ዘገባ |
| ቀ | የውሀማ ቅመራዎች/ዝግጅቶች ፒ-ኤች | መጠን/ዋጋ (ፈሳሽ ከሆነ) |
| | | |

| | | |
|---|---|---|
| በ | የ1% የውሀ ብረዛ ፒ-ኤች | ምርቶች በውሃ ውስጥ የመበረዛቸው አግባብነት ፡፡ መጠን/ዋጋ |
| ተ | ስስፔንስቢሊቲ/ኢመልሲብሊቲ | መረጃዎች ይቅረቡ |
| ቸ | የኦክሳይድ ባህሪያ | መረጃዎች ይቅረቡ |
| ኀ | ኮሮሲቭነስ | መረጃዎች ይቅረቡ |
| ነ | የውሃ ይዘት | መረጃዎች ይቅረቡ |
| ኘ | እርጥበታማነት | ተያያዥ መረጃዎች ያቅረቡ |
| አ | አረፋ ማውጣት | |
| ከ | የንጥል መጠን | |
| ኸ | ኢመልሲያቢሊቲ | |
| ወ | የኢመልሽን መረጋጋት | |
| ዐ | . ተለዋዋጭነት (የሄንሪ ህግ ቋሚ) | መጠን |
| ዘ | ዝልግልግነት | ዝግጅቶችን/ቅንብሮችን በጣም በዝቅተኛ መጠን ለመጠቀን ስለዝልግልግነትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ |
| ዠ | ሌሎች ባህሪዎች (የሚተገበር ከሆነ) | ለምሳሌ: ደረቅ/እርጥብ ወንፊት ሙከራ |
| የ | የምርመራ/የትንተና ዘዴ | ሙሉ ማጠቃለያ ዘገባ |

**በአባሪ 3 ለዋናው ንጥረነገር እና ለተዘጋጀው ፀረ-ተባይ የሚያስፈልጉ የቶክሲኮሎጂ ተዛማጅ ጥናት መረጃዎች**

| **ቶክሲኮሎጂ (የዋናው ንጥረነገር ቴክኒካል ግሬድ)** | | |
|---|---|---|
| ኤ.ዲ.አይ. | | |
| በአፍ በኩል በአጭር ጊዜ ምረዛ ለአይጥ/ለጥንቸል | | |
| በቆዳ በኩል በአጭር ጊዜ ምረዛ ለአይጥ | | |
| በቀጥታ በአፍ በኩል መጋለጥ ለአይጥ | | |
| የቆዳ መቆጣት ለጥንቸል | | |
| የአይን መቆጣት ለጥንቸል | | |
| የቆዳ መቆጣት በጊኒ አሳማ | | |
| መራባት | | |
| መለስተኛ የረጅም ጊዜ ቶክሲኮሎጂ | | |
| የረጅም ጊዜ ቶክሲኮሎጂ | | |
| ካንሰር የማስከተል አቅም በረጅም ጊዜ ( | | |
| በነርቭ ስርአት ላ ያው ቶክሲኮሎጂ | | |
| በጽንስ ላይ የለው ተጽእኖ | | |
| በዘረመል ላይ ያለው ተጽእኖ | | |
| ሜታቦሊዝም በአይጥ | | |
| ሌሎች ጥናቶች | | |

የተዘጋጀው ፀረ-ተባይ መረጃ ጠቋሚ

| | | ውጤት | የጥናቱ ውጤት አባሪ ቁጥር | ለቢሮ ባለሞያ ብቻ |
|---|---|---|---|---|
| **ቶክሲኮሎጂ** | | | | |
| ሀ. በአይጥ አጣዳፊ የአፍ | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| ለ. አጣዳፊ የቆዳ | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| ሐ.የእስትንፋስ | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| መ. የቆዳ መቆጣት | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| ሠ. የዓይን መቆጣት | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| ረ .የቆዳ መቆጣት በጊኒ አሳማ | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |
| ሰ. የአ.ጤ.ድ ምድብ | | | | |
| ሸ. ሌሎች የ መርዛማ ጥናት ውጤቶች<br>- ፀረ-ተባዮ ረጭ ተጋላጭነት ( የቆዳ መምጠጥ፣ የምናልባት በመስክ ሁኔታዎች ላይ ፀረ-ተባዮ ረጭ ተጋላጭነት)<br>- በየተዘጋጀው ፀረ-ተባይ ውስጥ ካሉ ሌሎች ንጥረ | 1. በአለም አቀፍ መመሪያ መሰረት( አዎ / አይደለም )<br>2. መመሪያው ተመላክቶዋል ( አዎ / አይደለም )<br>3. ጥሩ የላብራቶሪ ልምምድ መርሆዎች የተከተለ ወይንም በ ተሰራበት ሀገር በሚመለከተው አካል በታወቀ ቤተሙከራ የተሰራ (አዎ / አይደለም ) | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ነገሮች ጋር በተያያዥነት ያለው የቶክሲኮሎጂ መረጃ (በተዘጋጀው ፀረ-ተባይ ውስጥ ንቁ ያልሆኑ ተጨማሪዎች) | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3. የድንገተኛ የአደጋ ሂደቶች በአጋጣሚ ተጋላጭነት ወይም በመመረዝ ወቅት | | | | |
| ሀ. የሰው መመረዝ ምልክቶች | | | | |
| ለ. የመጀመሪያ እርዳታ ህክምና | | | | |
| ሐ. ለቆዳ ንክኪ | | | | |
| መ. ለአይን ንክኪ | | | | |
| ሠ. በመተንፈስ | | | | |
| ረ. በመመገብ | | | | |
| ሰ. ፀረ-መርዝ | | | | |
| ሸ. ማስታወሻ ለሐኪም | | | | |
| ቀ ኤም.አር.ኤል. ኮዴክ | | | | |
| በ የቅሪቱ አናሊሲስ ዘዴ | | | | |
| ተ. የቅሪትና እና የቅድመ-ሰብል ስብሰባ የጊዜ ክፍተት | | | | |

## በአባሪ 4 የአከባቢ ቶክሲኮሎጂ መረጃ

| ለዋናው ንጥረነር (ቴክኒካል ግሬድ) | ጥናቱ ተያይዞ ከቀረበ በዶዜ ውስጥ የተሰተው አባሪ ቁጥር | |
|---|---|---|
| 1. የአካባያዊ መርዛማነት<br>(ለዋናው ንጥረነር (ቴክኒካል ግሬድ) | | |
| 1.1 ለወፎች (2 ዝርያዎች) | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| 1.2 ለአሳ (2 ዝርያዎች) | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| 1.3 ለዳፍኒያ | | |
| | | |
| 1.4 ለአልጂ | | |
| | | |
| 1.5 ለንብ | | |
| | | |
| 1.7 ለመሬት ትላትሎች | | |
| 1.8 ለአፈር ጥቃቅን ፍጥረቶች | | |
| 2. በአካባቢ ውስጥ ያለው ጸባይ<br>ለዋናው ንጥረነር (ቴክኒካል ግሬድ) | | |
| በአፈር ውስጥ ያለው ጸባይ፣ የመጠን መቀነስ እና መጠኑ የሚቀንስባቸው መንገዶች) | | |
| 2.1. ዋና ዋና በኬሚካሉ ለውጥ የተገኙ ሌሎች ልውጥ ኬሚካሎች | | |
| 2.2 ዲ.ቲ.50 (በቀናት)$DT_{50}$ (days) | | |
| 2.3 ተንቀሳቃሽነት | | |
| 2.4 ጠጣር ነገር ላይ የመጣበቅ አቅም | | |

| | | |
|---|---|---|
| 2.5 የልውት ኬሚካሎች ተንቀሳቃሽነት | | |
| በውሃ  ውስጥ ያለው ጸባይ፣ የመጠን መቀነስ እና መጠኑ የሚቀንስባቸው መንገዶች) | | |
| 2.6.  ዋና ዋና በኬሚካሉ ለውጥ የተገኙ ሌሎች ልውጥ ኬሚካሎች | | |
| 2.7 ዲ.ቲ.50 (በቀናት) | | |
| 2.8 ለመሬት ውሃ | | |
| 2.9 ለጉድጓድ ውሃ | | |
| 3. በእጽዋት ውስጥ የሚፈጠር ቅሪት | | |
| 3.1  ዋና ዋና በኬሚካሉ ለውጥ የተገኙ ሌሎች ልውጥ ኬሚካሎች | | |
| 3.2  ሜታቦሊዝም | | |
| 3.3  የቅሪቶች ጸባይ | | |
| 3.4  የሰብል አይነት | | |

አባሪ 5

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን (የፀረ ተባይ ፍቱንነት ሙከራ ፈቃድ)

ቁጥር.......................

ቀን.........................

የድርጅቱ ስም______________________________________________________

አድራሻ __________________________________________________________

የአመልካች ስራ ዘርፍ (አምራች፣ አስመጪ፣ ወኪል፣ እንደራሴ ወይም ሌላ) __________________________

የዋና ንጥረ ነገር አምራች ስም.._________________________________________________

የዋና ንጥረ ነገር አምራች አድራሻ ( መገኛ ቦታውን ጨምሮ በዝርዝር) ______________________________

የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ______________________________አድራሻ (ስ.ቁ) _______________________________________

<u>የምርቱ ዝርዝር መግለጫ</u>

| ተ.ቁ | ንግድ ስም | ዋና ንጥረ ነገር እና ይዘት መጠን | ኢላማ ተባይ | ሙከራ የሚካሄድበት ሰብል ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

<u>የሙከራ ዓይነት</u>

ፀረ ነፍሳት ☐ ፀረ ሻጋታ ☐ ፀረ አረም ☐ ፊሊቲ ☐

የመጋዘን ተባዮች ☐ ፀረ ወባ ☐

ሙከራውን እንዲያከናውን የተመረጠው ተቋም __________________________________________

ሙከራው እንዲካሄድበት የተመረጠው አካባቢ __________________________________________

ሙከረው የሚካሄድበት የሰብል ዝርያ _______________________________________________

የተመራማሪው ስም _________________________________________________________

የተመራማሪው ረዳት ________________________________________________________

ሙከራው የሚጀመርበት ቀን ____________________________________________________

<u>አባሪ ሰነዶች</u>

የምርት አያያዝ ሰነድ ☐

የመግባቢያ ስምምነት (በምርምር ተቋም እና በአስመዝጋቢ መካከል የሚደረግ) ☐

ቴኪኒካል ማንዋል ☐

የንግድ ውክልና ስምምነት (በአምራቹ እና በአስመዝጋቢው መካከል የሚደረግ) ☐

የምርምር ዕቅድ (በተመራማሪው የሚዘጋጅ) ☐

አባሪ 6

# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
## የፀረ ተባይ ናሙና ማስገቢያ ፈቃድ መጠየቂያ ቅፅ

የአመልካቹ ስም እና አድራሻ ____________________________________________________________

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

አመልካች የስራ ዘርፍ (አምራች፣ አስመጪ፣ ንግድ ወኪል፣ እንደራሴ ወዘተ ) _________________

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የአምራች ስምና አድራሻ ________________________________________________________________

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የዋና ንጥረ ነገር አምራች ስምና አድራሻ ____________________________________________________

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የድረጅቱ ተወካይ ስም ______________________________ ስልክ _________________________

<u>የፀረ ተባዩ ዝርዝር መግለጫ</u>

| ተ.ቁ | የፀረ ተባይ ነግድ ስም | የዋና ንጥረ ነገር ዓይነት እና ይዘት መጠን | መጠን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት (ቁጥር) | ይዘት (ሊትር) | ክብደት (ኪግ) |
| | | | | | |
| | | | | | |

ፕሮፎርማ ኢንቮይስ ቁጥር ________________________ የዝጅት መጠን እና አይነት ______ የማሸጊያ ዓይነት ____
የሚመጣበት ሀገር ______________________________

ሙከራው የሚካሄድበት አካባቢ ________________________________________________________ ናሙናው ሀ
የአያያዝ ደህንነት ሰነድ ☐

የመግባባያ ስምምነት (ከምርምር ተቋሙ ጋር የተደረገ) ☐

ያፀረ ተባዩ የቴኪኒክ መመሪያ ወይም የምርት መለያ (በ አምራቹ የሚዘጋጅ) ☐ የውክልና ስምምነት (ከአምራቹ
ስም ________________________

ፊርማ ________________________

አባሪ 7

**አባሪ 7 የፀረ-ተባይ ምርት መለያ እና በራሪ ወረቀት**

1. **የፀረ-ተባይ መለያ ይዘት**
2. በመያዣው ላይ ያለው የፀረ-ተባይ መለያ የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፡፡

- የንግድ ስም፡
- የዋናውን ንጥረ ነገር መጠንና የዝግጅቱን ዓይነት፡
- የፀረ-ተባዩን መግለጫና ዋና ጥቅሙ፡
    - ፀረ-ተባዩ የሚቆጣጠረው ተባይ፡ ፀረ-ተባዩ የሚረጭበት ሰብል እና በማመለከቻው ላይ እና በውጤታማነት ሪፖርቱ ላይ በተገለፀው መሰረት የርጭት መጠን
- ተባዩን በሚቆጣጠርበት አሰራር ላይ ተመስረቶ ለፀረ-ተባዩ የተሠጠ ምደባ
- የማስጠንቀቂያ መልእክት፡

| |
|---|
| **ፀረ-ተባዩን ከመጠቀምዎ በፊት መለያውንና በራሪ ወረቀቱን ያንብቡ** |

| |
|---|
| **ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ በጥንቃቄ ተቆልፎ ይቀመጥ** |

- የአምራቹ ስም፡
- የመጀመሪያ ወኪሉ ወይንም የአስመጭው ስም፡
- የምዝገባ ቁጥር፡
- የተመረተበት ቀን፡
- አገልግሎቱ የሚያበቃበት ጊዜ፡
- የምርት ባች ቁጥር፡
- የማሸጊያው የተጣራ ይዘት፡
- ሥእላዊ መግለጫ፡
- የዓለም ጤና ድርጅት የቀለም መለያ፡
- የአደጋ ምልክት፡
- የአደጋ መግለጫ፡

## 3. በራሪ ወቀት ሊይዛቸው የሚገቡ መረጃዎች

- ደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎች
- አከመቻቸት፡
- የአወጋገድ ዘዴ፡
- የመመረዝ ምልክት
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ፡
- የባለሙያ መረጃ፡
- የአጠቃቀም መመሪያ፡_/የድብልቅ አዘገጃጀት፡ የርጭት መጠን፡ ፀረ-ተባዩ ከሌሎች ፀረ-ተባዮች ጋር የሚኖረው የመዋሀድ ባህሪ ፡ የመሬት ላይ ርጭት እና በአየር ርጭት፡ /አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት/
- ፀረ-ተባዩ ከተባዩ ጋር እንዳይላመድ የሚደረግ ጥንቃቄ፡
- ለሚከተለው ሰብል የመቆያ ጊዜ፡ /አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት/፡
- በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት፤
- ሰብሉ ፀረ-ተባዩን የመቋቋም ብቃት፡
- የፀረ-ተባዩ የቁጥጥር ዘዴ፡
- ከርጭት በኋላ ማሳ ውሥጥ ተመልሶ ለመግባት የቆይታ ጊዜ፡
- ከርጭት በኋላ ሰብሉን ለመሰበሰብ የሚያስፈልግ ጊዜ፡
- ህጋዊ ሃላፊነት፡

4. ባለአንድ ፓናል የፀረ-ተባይ መለያ

| |
|---|
| **ፀረ-ተባዩን ከመጠቀምዎ በፊት መለያውንና በራሪ ወረቀቱን በጥንቃቄ ያንብቡ** |
| የንግድ ስም፡<br><br>የዋናውን ንጥረ ነገር መጠንና የዝግጅቱ ዓይነት፡ |
| የፀረ-ተባዩ መግለጫና የተጠቃለለ ጥቅሙ፡ |
| የፀረ-ተባዩ ምደባ /ፀረ-ተባዩ ተባዩን በሚቆጣጠርበት አሰራር መሰረት/ |
| **ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ በጥንቃቄ ተቆልፎ ይቀመጥ** |
| የምዝገባ ቁጥር፡ |
| አምራች/አዘጋጅ |
| የመጀመሪያው ወኪል ፣ወይንም የአስመጭው ስምና አድራሻ |
| የተመረተበትን ቀን፡ |
| የሚያበቃበት ቀን ፡ |
| የባች ቁጥር |
| መጠን |
| ስእላዊ መግለጫ<br><br>የአደጋ ምልክት /በዓለም ጤና ድርጅት ምደባ መሰረት/ የአደጋ መግለጫ<br><br>/በየዓለም ጤና ድርጅት የአደጋ ምደባ መሰረት የቀለም ዓይነቱ መለያው ከሚይዘው ቦታ ከአስራ አምስት ከመቶ ማነስ የለበትም/ |

5. ባለሁለት ፓናል የፀረ-ተባይ መለያ

| ፀረ-ተባዩን ከመጠቀምዎ በፊት መለያውንና በራሪ ወረቀቱን በጥንቃቄ ያንብቡ | | |
|---|---|---|
| ደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎች<br><br>• አከመቻቸት:<br>• የአወጋገድ ዘዴ:<br><br>የማስጠንቀቂያ መልእክት:<br><br>የመመረዝ ምልክቶች:<br><br>የመጀመሪያ እርዳታ:<br><br>ለሀኪም ምክር:<br><br>(ማርከሻ መድኃኒት ካለ ይገለፅ )<br><br>ፀረ-ተብዩን የመቋቋም ማስጠንቀቂያ:<br><br>የአጠቃቀም ገደብ:<br><br>ለሚከተለው ሰብል የመጠበቂያ ጊዜ:<br><br>/አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት/ | የንግድ ስም<br><br>የዋናውን ንጥረ ነገር መጠንና የዝግጅቱን ዓይነት:<br><br>የፀረ-ተባዩ መግለጫና የተጠቃለለ ጥቅሙ:<br><br>የፀረ-ተባዩን ምደባ /ተባዩን በሚቆጣጠርበት መንገድ/<br><br>**ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ ተቆልፎ በጥንቃቄ ይቀመጥ**<br><br>• የምዝገባ ቁጥር<br>• የአምራቹ ስም<br>• የመጀመሪያው ወኪል ፣ወይንም የአስመጭው ስምና አድራሻ<br>• የተመረተበትን ቀን:<br>• አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን:<br>• የምርት ባች ቁጥር:<br>• የተጣራ ይዘት: | የአጠቃቀም መመሪያ:<br><br>• <u>የድብልቅ አዘገጃጀት:</u><br>• <u>የርጭት መጠን:</u><br><br>ፀረ-ተባዩ ከሌሎች ፀረ-ተባዮች ጋር ያለው የመዋሀድ ባህሪ :<br><br>የመሬት ላይ ርጭት:<br><br>በአየር ርጭት:<br><br>/አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት/<br><br>ከርጭት በኋላ የቆይታ ጊዜ:/አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት/<br><br>ከርጭት በኋላ ሰብሉን ለመሰበሰብ የሚያስፈልግ ጊዜ:<br><br>ህጋዊ ሃላፊነት: |

**ስእላዊ መግለጫ** **የአደጋ ምልክት በዓለም የጤና ድርጅት ምደባ መሰረት** **የአደጋ መግለጫ**

**/በየዓለም የጤና ድርጅት የአደጋ ምደባ መሰረት የቀለም ዓይነቱ መለያው ከሚይዘው ቦታ ከአስራ አምስት ከመቶ ማነስ የለበትም/**